

# ሩት

* መሳፍንት ምድሪቱን በሚያስተዳደሩበት ወቅት በምድሪቱ ላይ ኃይለኛ ድርቅ ሰፍኖ ነበር። ከዚህ የተነሳም አቢሜሌክ የሚባል ሰው ሚስቱን ኑሃሚንንና ሁለቱን ወንዶች ልጆቹን ይዞ ወደ ሞአብ ምድር ተሰደደ። በዚያን ጊዜ በሞአብ ምድር እህል ነበርና ነው።

* አቢሜሌክ ሞተ። ኑሃሚንም ከበሏ ሞት በኋላ ከሁለት ልጆቿ ጋር ቀረች። አንደኛው ኦርፋ የምትባል ሞአባዊት ሲያገባ ሌላኛው ደግሞ ሩት የምትባል ሞአባዊት አገባ። ከአስር አመት በኋላም የኑሃሚን ሁለቱ ልጆቿ ሞቱ። ኑሃሚንም ወደ ቤተልሔም ለመመለስ ወሰነች።

*. ሁለቱ የልጆቿ ሚስቶች ከእርሷ ጋር ለመመለስ ቢወስኑም እርሷ ግን በሞአብ ምድር እንዲቀሩ ነገረቻቸው። ሩት ግን ከኑሃሚን ጋር ለመሄድ ቆረጠች። ስለዚህ ሁለቱ ወደ ቤተልሔም ሄዱ። የኑሃሚን ጓደኞች ኑሃሚን ተመልሳ በመምጣቷ በጣም ተደሰቱ።

* እንደ እግዚአብሔር ሕግ በዚያን ዘመን አንድ ገበሬ ምርት ሲሰበስብ በመሬት ላይ የሚወድቀውን እህል አይሰበስብም።እዚያው ይተወውና ድሆች ለቅመው ይጠቀሙበታል። እንደዚህ አይነቱ በመሬት ላይ የወደቀ እህልን መሰብሰብ ቃርሚያ ተብሎ ይጠራል። ሩትም በቦኤዝ እርሻ ለመቃረም ሄደች። ቦኤዝ የኑሃሚን ቤተሰብ ዘመድ ነበር። ሩትም በዚያን ቀን ከቦኤዝ እርሻ ለእርሷና ለኑሃሚን የሚበቃ ብዙ ቃረመች። ቦኤዝም እንዴት ጠንክራ በቃርሚያ ስራ ላይ እንደተሰማራች አየ። በእርሱ እርሻ ላይም እንድትቆይ ፈቀዳለት። ከእርሱ ጋር እንድትበላም ጋበዛት። እንዲሁም ምንም ጉዳት እንደማይደርስባትና እንደሚጠብቃት ነገራት።

* ቦኤዝ ሩትን ማግባት ፈለገ። ነገር ግን ከቦኤዝ ይልቅ ሩትን የማግባት መብት የነበረው ሌላ ሰው ነበር። ሁለቱ ሰዎች ተገናኙ። ሌላኛው ሰውም ሩትን ለማግባት እንደማይፈልግ አስረዳ። በወቅቱ እንደነበረው ልማድም ጫማውንም አውልቆ አራገፈና ውሳኔው ትክክለኛ ውሳኔ መሆኑን ገለፀ። ስለዚህ ቦኤዝ መሬቱን ገዝቶ ሩትን እንዲያገባ ነገረው።

* ቦኤዝና ሩትም ኦቤድ የሚባል ልጅ ወለዱ። ኦቤድም ካደገ በኋላ እሴይ የሚባል ልጅ ወለደ። እሴይም ዳዊት የተባለ ልጅ ወለደ። የሩት የልጅ ልጅ የሆነው ዳዊትም የእስራኤል ንጉስ ሆነ።

ይህ የሩትና የኑሃሚን ታሪክ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን በመፅሐፈ ሩት ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 4 ድረስ ነው።

http://gardenofpraise.com